# የሚያስገርመው የእሁድ ምሽት

ከበልጅግ አሊ

-፩-

ቀኑ እሁድ ነው ። እንደተለመደው በዚህ የእረፍት ቀን ስለሃገራችን ወቅታዊ ሁኔታዎች ለማወቅ ድረ ገጾችን ማገላበጥ የማይቀር ነው ። ከድረ ገጽ ወደ ድረ ገጽ ስረማመድ የተስፋዬ ገብረ አብን " የስዬ ምስጢሮች"ጽሁፍ አነበብኩ ። ጽሁፉ ያተኮረው ስዬ በጻፈው መጽሐፍ ላይ ነው ። ጽሁፉ የስዬን ውሸቶች በሰፊው ያጋልጣል ።

ስለ ወያኔ አባላት ውሸት ስንሰማ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያችን አይደለም ።ተስፋዬ ገብረ አብ አሁን ይረዳው እንጂ ወያኔ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ ውሸት ቀለቡ ነው ።ተስፋዬን ዛሬ እንዲህ ያስጠላውን ውሸት ለብዙ ዘመናት ሲነገር የሰማን ሰዎች ብዙም አያስደንቀንም ።እንዲያውም የወያኔን ውሸት በሚመለከት ብዙ ቁም ነገር ያዘሉ ቀልዶች በአሁኑ ወቅት እየተፈጠሩ ናቸው ። እስቲ አንዱን ላጫውታችሁ ።

ንግሥቲቱ የመለስ ሚስት አዜብ ገሃነም እሳት ለመጎብኘት ትሄድና ብዙ የግድግዳ ሰዓት ትመለከታለች ። በመደነቅ ይህ ሁሉ ሰዓት ምንድነው ? ብላ ትጠይቃለች ። ሰዓቱ የእያንዳንዱ ሰው ውሸት መጠን መለኪያ ነው ትባላለች ። ስትፈልግ ትቆይና የመለስን ሰዓት ስላላገኘችው ሰዓቱ የት እንደሄደ ትጠይቃለች ።የሚስጎበኛት ሳቅ ብሎ ከውሸቱ ብዛት በጣም ስለሚሽከረከር እንደ ንፋስ መስጫ ( ቬንትሌተር ) ለመጠቀም ወደ ላይ ወስደነው ነው ብሎ መለሰላት ። ለዛሬው ይብቃን እንጂ ብዙ ቀልዶች በወያኔ ውሸት ተፈጥረዋል ።

ለነገሩ ነው እንጂ ስዬ ብቻ አይደለም ብዙዎቹ የዘንድሮ ፖለቲከኞች እንኳን ለንባብ የሚበቃ ጥሩ መጽሐፍ መፃፍ ቀርቶ የተጻፈውንም ማንበብ እንደማይወዱ ከተረዳሁ ሰንብቻለሁ ። ስዬ መጽሐፍ ብሎ ባወጣው ላይ ቢቀባዥር አይደንቀኝም። የዘንድሮ ፖለቲከኞች እንኳን በአንድ መጽሐፍ ውስጥ በአንድ ቃለ መጠይቅ ላይ በመጀመሪያ የተናገሩትን በስተመጨረሻ ይረሱት የለም ? እንደዚህ ዓይነት ግለሰቦች ወደው አይመስለኝ። በመጀመሪያ የሚያወላውል አቋም ሲኖር ለውሸት ይዳርጋል ። በሁለተኛ ውሸት ደግሞ ይረሳል።

ይህንን ጉዳይ ሳሰላስል አንድ ቀልድ ትዝ አለኝ ።ሰውዬው አገሩ ወደ ሻሸመኔ ነው ። በጣም ውሸታም ሲሆን ለምስክርነት ተጠርቶ ፍርድቤት ቀርቦ ነበር ። የሰውዬውን ውሸታምነት የሚያውቅ ጠበቃ ስምህ ማነው? ብሎ ይጠይቀዋል ። ከበደ ይላል ።አገርህ የት ነው ሲለው ደብረዘይት አለ ። ጎበዙ ጠበቃ ሌሎች ነገሮች ሲጠይቅ ይቆይና ተመልሶ አገርህ የት ነው ብሎ ይጠይቀዋል ። ያ ውሸት የለመደ ምስክር ከላይ ደብረዘይት ማለቱን ይረሳና ናዝሬት ይላል ። ይህንን በጽሞና ይከታተሉ የነበሩ ዳኛ ቆጣ ብለው " ምነው ጃል ቅድም ደብረዘይት ብለኸን" ሲሉ ጎበዙ ጠበቃው ቀበል ያደርግና "ምነው ጌታዬ ባይቸኩሉብኝ አገሩ ሻሸመኔ ሳላደርሰው አልቀርም ነበር " አለና ዳኛውን አሳቃቸው ።

የስዬም ጉዳይ ከዚህ የተሻለ አይደለም። ፈርን ተከትሎ ባልተፃፈው መጽሐፍ ውስጥ ስዬ ራሱን ከማጋለጡ በፊት ከጥንት ከጥዋቱ ብዙዎች ታዛቢዎች፣ በሳል ፖለቲከኞች የተነናገሩት እንደነበረ መረዳት ይኖርብናል ። ስዬና መሰሎቹ በውሸት ውስጥ ተዘፍቀው ስለኖሩ ወደ እውነቱ ለመምጣት ያዳግታቸዋል። ለወያኔዎች መዋሸት የቀን ተቀን ኑሯቸው ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይጨነቁ ይችላሉ ። ግን አንባቢያን መልስ ይጠብቃሉ ። በአደባባይ የተዋሸ በአደባባይ መመለስ አለበት ።ይህ ብቻ አይደለም ከስዬ የምንጠብቀው ገና ብዙ መልስ አለ ። የነ ጸጋዬ ደብተራውን ጉዳይ ለዴሞክራሲ የቆሙ ሁሉ እውነት ብቻዋን አደባባይ ላይ ጎልታ እስክትታይ ድረስ ጥያቄ ማቅረባቸውና ስለፍትህ መጮኸቸውን አያቆሙም ።የነዚህ ንፁሃን ደም ፣ የእነዚህ የኢትዮጲያ ልጆች መድረሻ አሁንም ተዋሽቶ መታለፍ የለበትም ።ፀጋዬና ሌሎቹ ቁጥራቸው የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን በትግራይ ጉድጓድ ውስጥ ተቀብረው በገሃነም እሳት ውስጥ ሲኖሩ እነ ስዬ ደግሞ መኪና እየቀያየሩ ፣ በድሎት እየተንደላቀቁ መኖራቸው ሳያንሳቸው በተቃዋሚ ጎራ ሆነውም እውነትን ለመደበቅ የሚያደርጉት ተንኮል ቀኑን ጠብቆ ይጋለጣል ። ነገ ተነገ ወዲያ በጥቅም ሲጣሉ የምንሰማው ሊሆን ይችላል ። ግን ለእነዛ በድብቅ እስር ቤት በመከራ ለሚማቅቁ ደቂቃም እድሜ ነች ። ስለዚህ እነ ስዬና መሎቻቸው በሚጽፏቸው ውሸት በተሟላ ተረት ተረት ተታልለን ዝም ልንል አይገባም ።እነዚህ ሥልጣንን ተገን አድርገው ብዙ ግፍና በደል የፈፀሙ ግለሰቦች በፍትሕ ፊት ሊቆሙ ይገባቸዋል ።

ይህ ብቻ አይደለም ከነ ስዬና ከወያኔ ጋር ሲሠሩ ከነበሩት የምንጠብቀው። ከዚህ ቀደም ገብረመድህን አርአያ ለቢቢሲ ሪፖርት ያጋለጠውን የድርቅ ገንዘብ ጉዳይ ወያኔን በመርዳትና በመዋሸት እውነቱን በመደበቅ ተድበስብሶ እንዲቀር ማድረጋቸው ሊዘነጋ እንዴት ይቻላል ? ያ ምግብ አጥቶ በረሃብ የሞተ ኢትዮጵያዊ ዛሬም በምድረ ከርስ ውስጥ ሆኖ አሁንም ስለእውነት ይጮኻል ።ዛሬ በዓለም ጦር ፍርድቤት እነ መለስን ሊያስጠይቅ የሚችለውን ጉዳይ በእነ ስዬ እውነትን የመደበቅ ዝምታ ተሸፋፍኖ ይገኛል።እነ ሰዬ ወያኔ ከስልጣን እንዲወርድ የሚፈልጉ ቢሆኑ ኖሮ ብዙ ሊፈነዱ የሚችሉና ወያኔን ሊያጠፉ የሚችሉ ምሥጢሮችን በመደበቅ ወንድማቸው ሲታሰር ለማስፈታት ብቻ አይጠቀሙበትም ነበር ። ይህ በመለስና በእነ ስዬ የተጀመረው የእከክልኝና ልከክልህ ትብብር ሊቆም ይገባል።

"የስዬን ምስጢሮች "አንብቤ ስጨርስ እነ ስዬ ምን ይመልሱ ይሆን ብዬ ማሰቤ አልቀረም ። ለአንድ ወዳጄ ስለዚህ ጉዳይ ልነግረው ብደውል ለካ ቀድሞኝ መልሱንም ጨምሮ አንብቦ ደረስኩ ። ኢትዮሚዲያ ላይ መልሱ እንዳለ ስለነገረኝ በቶሎ በጉጉት ወደዚያ አመራሁ ።"**አርበኞች ግንባር (ክፍል 4) ሻዕብያ ፣ግንቦት 7 ፣አንዳርጋቸው ጽጌ እና የሻዕብያው ሰላይ ተስፋዬ ገብረአብ "( የጥቁር ሜካ ሪፖርት** ) በሚል ተቀምጧል ።ጽሁፉ ከድጡ ወደ ማጡ እንደሆነ ለመረዳት አዳጋች አይደለም ።ከኢሳያስ ተጽእኖ ወጣን ብለው የሚጮኹ ግለሰቦች በስዬ አሰብን እናስመልሳለን የሚል ቀቢፀ ተስፋ ውስጥ መነከራቸው የሚያሳዝን ነው ።

ዛሬ ስለ ሻዕብያ መጥፎነት ይህንን የሚጽፉ በሞላ ስለ ኢሣይስ አፈወርቂና ስለ ሻዕብያ ፀረ ኢትዮጵያ ዓላማ ስንት ጊዜ ሲነገሩ እንቢ በማለት እንዲያውም አልፈው ተርፈው ሲሳደቡ የነበሩ ፣ አሁን እርስ በርስ ሲጣሉ የሕዝብ ድጋፍን ለማግኘት እንዲህ ነው ቢሉ የሚያምናቸው ለማግኘት ይከብዳቸዋል ። ስለ አርበኞች ግንባር የተጻፈውን ስገመግመው ምንም እንኳ ስለ ሻዕብያ የፃፉትን ሃሳብ ብጋራቸውም ዛሬ ያንን አጀንዳ ያነሱበት ምክንያቱን ልስማማ አልችልም ። እውነት ሃሳባቸው ያ ከሆነ ከማንም ጋር ሳይወግኑ ለኢትዮጵያ የሚበጀውን መፃፍ እንጂ የስዬ ተከላካይ መሆን አይገባቸውም ። ስዬም ቢሆን ለኤርትራ መገንጠል ከኢሳያስ ጋር የጨፈረ ነው። ስዬ ዛሬም ቢሆን ከሻዕብያ ጋር በመሆን የሠራውን ተንኮል በሙሉ አላጋለጠልንም ። በተለይ ደግሞ ይህንን ጠብ በማጋጋል የእነ ስዬንም ብሎም የወያኔንም ሆነ የኢሳያስን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚራወጡትን ልናወግዛቸው ይገባል ።

ለነገሩ ዋናው የጠቡ መነሻ ምን እንደሆነ ለማወቅ አንድ ጽሁፍ ላይ የቀረበ ምክንያት ብቻ በቂ አይሆንም ። ይህ በጸረ ወያኔ ትግል ውስጥ የተለምደ ነው ።ብዙ ድርጅቶች ተከፋፍለዋል ፣ ምክንያታቸውን ደርድረዋል ፣ ፓልቶክ ላይ ቀርበዋል፣ ደጋፊ ለማግኘት ጥረዋል ፣ የተቃራኒያቸውን ስም አጥፍተዋል ። እውነቱ ግን እያደር ነው የሚታወቀው ። ብዙው ጊዜ እንዲዘህ ዓይነት ጠብ ሲነሳ የጠቡ ምክንያትና በአደባባይ የሚነገረው የትዬለሌ ናቸው ።ለማንኛውም ሁኔታውን ለማጣራት ወደ ፓልቶክ ብቅ አልኩ ። ፓልቶክ እንደ ስዬ ምስጢር የለውም ። ሁሉንም ግልጥልጥ አድርጎ በጥሩውም ፣በመጥፎውም ፣በእውነቱንም በውሸቱም ያሳየናል ።ማገናዘብ ግን የግላችን ነው ።

በምሽቱ ከረንት አፌርስ የፓልቶክ ክፍል የአርበኞች ግንባር የውጭ አላፊዎችን ጋብዘው ነበር ።እነዚህ የተጋበዙት ሰዎች በኢትዮ ሚዲያ ላይ የተጻፈውን ።"**አርበኞች ግንባር (ክፍል 4) ሻዕብያ ፣ግንቦት 7 ፣አንዳርጋቸው ጽጌ እና የሻዕብያው ሰላይ ተስፋዬ ገብረአብ "( የጥቁር ሜካ ሪፖርት** ) የሚቃወሙና እውነት ነው የሚሉትን ለማስረዳት የቀረቡ ናቸው ። ጆሮዬን እስከሚያመኝ ሰማሁ ። የችግሩና የመከፋፈሉ ዋና መሪዎች ናቸው የተባሉትን ስስማ የበለጠ ግራ ገባኝ ። ኤልያስ ክፍሌ የኢትዮጵያ ሪቪው ዋና አዘጋጅና ከእሱ ጋር ወደ ኤርትራ ሄዶ የነበረውና ስለሺ ጥላሁን ተጠቀሱ ። እውነቱም ቀኑ አብዷል ሰው ብቻ አይደለም ። የጉድ ሃገር ገንፎ እያደር ይፋጃል እንዲሉ ።ኤሊያስ ክፍሌ ትላንት ኢሳያስ አፍወርቂን የዓለም አንደኛ ዴሞክራት፣ ከሁላችን በላይ ለኢትዮጵያ አሳቢ ብሎ እንዳላለ ከምኔው ተቀይሮ እንዲህ ሆነ ? ሌላ ሰለሞን ተካልኝ ሊሸተን ነው እንዴ? ካልሆነ ግን ለሕዝብ ጉዳዩ ግልጽ መሆን ሲገባው በተወካይ እስከመቼ እንደሚጣሉ አይገባኝም። . . . . .ሌላ አንድ ቀልድ ትዝ አለኝ ።

ገበሬው በቆሎ ይዘራል ። ጦጣ ከላይ ሆና ትመለከታለች ። ጦጣ ምንም እንዳላወቀች ትሆንና ገበሬ ምንድነው የምትዘራው ? ብላ ትጠይቃለች ። ገበሬው በቆሎውን አውጥታ እንዳትበላበት ሰሊጥ ነው ይላታል ። ጦጣዋ ሳቅ ብላ ልናይ ኋላ አለች ይባላል።

እንግዲህ የሰሞኑን የፖለቲካ ማእበል የሚረጋው በጊዜ ነው ። ማን ከማን እንደሚቆም ፣ ማን እንደሚከድ ፣ ማን ምን እንደሚያጋልጥ፣ ማን ወያኔ ጋ እንደሚገባ ለማወቅ መጠበቅ ነው ። ጠቡ በሻዕብያና በወያኔ መካከል ሲሆን ከፋፋዮችም ፣ዘረኞቹም፣ ተገጣዮዎቹም ከጀርባ ናቸው ።ኢትዮጵያውያን በዚህ ጉዳይ መጎዳታቸው የማይቀር ነው ። ከወያኔ ዘረኛ መንግሥት ሃገራችንን ነፃ እናወጣለን ብለው ያገኙትን መንገድ ለመጠቀም የበሰሉ ፖለቲከኞችን ምክር ሳይሰሙ ወደ ኤርትራ የሄዱትን የዋህ ወንድሞቻችንን የዝሆኖቹ ጠብ እንደሳሩ እንዳያጠፉቸው ፍርሃት በእያንዳንዳችን ሊያድር ይገባል ። የጠቡ ተሳታፊዎችም በግልፍተኝነት የሚናገሩት ሊያመጣ የሚችለውን ጉዳትን መመዘን ይገባቸዋል ። አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ ሲባል የሚፈተልከው ምስጢር ለወያኔ ሊጠቅመው ይችላል ። አሁንም እየጠቀመው ነው ።

ወደ ምሽቱ ሌላ ቃለ መጠይቅ ተከታተልኩ ዶክተር ወንድሙ አዲስ ሰለ አቋቋሙት ሕብረት መግለጫ ለመስጠት ተጋብዘው ቀረበው ነበር ። ከቃለ መጠይቁ እንደተረዳሁት በዚህ አዲስ በተቋቋመው ሕብረት ውስጥ ፡-

፩ኛ .በቅርብ በግንቦት ሰባትና አጋሮቹ የተመሰረተው አዲሱ ሕብረት በዚህኛው እሳቸው በመሰረቱት የአዲሱ አዲሱ ሕብረት ውስጥ የለበትም።
2ኛ. ሃገር ቤት ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ወያኔ የሚያደርስባቸውን ጥቃት በመፍራት ሕብረቱ ውስጥ አይገቡም ።
3ኛ. የኢሕአፓ ጉዳይ በእሳቸው አባባል ገና ሕብረቱ ውስጥ ይግባ አይግባ አይታወቅም።

እንግዲህ እነዚህን ሁሉ ድርጅቶች ለማሰባሰብ ከዶክተር ወንድሙ ብዙ ሥራ ይጠበቃል ። ለዶክተር ወንድሙ ሥራ መሳካት የምንመኝ ሁሉ የዘወትር ፀሎታችን መሆን የሚገባው

1. በግል ራሳቸውን ለማሳወቅ ከሚጥሩ፣ለሥልጣን ከሚቋምጡ ግለሰቦች፣
2. ሌላውን ድርጅት ለማጥፋት ዶክተሩን መጠቀም ከሚፈልጉ ፣
3. በስም ላይ ቅጥያ እየጨመሩ ታሪክን ከሚያጎድፉና ድርጅት ከሚፈለፍሉ ፣
4. በድብቅ የወያኔን ዓላማ ከሚያራምዱ ባንዳዎች ፣
5. የግለሰብ ከሆኑ ድርጅቶች ፣እንደ አሸን ስም ሳይቀይሩ ከተፈለፈሉ ድርጅቶች
6. በኢትዮጵያ አንድነት ከማያምኑ ድርጅቶች ፣
7. በደርግ ጊዜም ሆነ በወያኔ የፈፀሙትን ወንጀል ለመደበቅ ከሚራወጡ
8. ከውጭ መንግሥታት የሚገኝን ገንዘብ ለመቀራመት ከተቋቋሙ የሲቪክ ድርጅቶች ፣
9.

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጠልፈው ጥለው ካሰቡት ዓላማ ሳይደርሱ እንዳያሰናክሏቸው የሚያምኑበት ከራማ ይጠብቃቸው ብለን ነው።የእሁዱን ቃለ መጠይቅ የተከታተሉና እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸውን ሁኔታዎችና ሊፈጥሩ የሚችሉት ችግር ያልተረዱ ያሉ አይመስለኝም ። ምንአልባት ከተገኙ ለእሱም እውቀቱን ይገልጽላቸው ዘንድ እንጸልይ ።

የሚስገርመው የእሁድ ምሽት በዚሁ አለቀ ። የሚቀጥለውን እሁድ ደህና ያድርግልን ።

ሰለኢትዮጵያ አንድነት የሚያስቡ በሰላም ይክረሙ !!
beljig.ali@gmail.com

መስከረም 2003